# በአገር አቀፍ የትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች ኤጀንሲ
# የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ብሄራዊ ፈተና አስመልክቶ የተሰጠ
# ጋዜጣዊ መግለጫ

## የ2011 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ የ12ኛ ክፍል ፈተና ነሐሴ 7 ቀን 2011 ዓ.ም. ይፋ ተደረገ፡፡

በ2011ዓ/ም ዓመታዊ የትምህርት ሰሌዳ መሰረት የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ (የ12ኛ ክፍል) ፈተና መሰጠቱ ይታወሳል፡፡ ከቅርብ አመታት ወዲህ ብሄራዊና ክልላዊ ፈተናን ደህንነት በማስጠበቅና የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ በመንግሰት ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሰረት ፈተናውን በሰላማዊ መንገድ ለማከናወን በመንግስትና በህዝቡ ሰፋፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በተለይም ተግባሩን በጠራ ዕቅድ የመምራትና የህብረተሰቡን ግንዛቤና ባለቤትነት የማሳደግ ብሎም ከማዕከል እስከ ትምህርት ቤት በተደራጀ ግብረሃይል መምራት ተችሏል፡፡

በዚሁ መሰረት ባለድርሻ አካላትና መላው ህዝብ ባደረጉት ርብርብ እጅግ በተረጋጋ የፈተና አካባቢ ፕሮግራሙን በማሳካቱ የአመቱ የፈተና አስተዳደር ስራው መሻሻል አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ኤጀንሲው በፈተና አስተዳደሩ ሂደት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ የፌዴራልና የክልል ተቋማት፣ ለፈተና አስፈጻሚዎች፣ ለመላው ተፈታኝ ተማሪዎች፣ የተማሪው ወላጆች እና በሂደቱ ለተሳተፉ ባለድርሻ አካላት በሙሉ ከፍተኛ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

ኤጀንሲውም የፈተና ደህንነትን የማሰጠበቅ ስራውን ከፈተና ዝግጅት እስከ ውጤት ገለፃ ለማሰቀጠል በመስራት ላይ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ኤጀንሲው ፈተናው በተሰጠበት ወቅት የፈተና ህግ ጥሰት መፈፀማቸው በወቅቱ ከቀረቡ ሪፖርቶችና ተያያዥ መረጃዎች በመረጋገጡ የ68 ተፈታኞች ውጤት ሙሉ በሙሉ እንዲሰረዝ አድርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኤጀንሲው በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብ/ብ/ህ፣ አማራ እና ቤንሻንጉል ክልሎች በሚገኙ የተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 846 ተፈታኞች የተወሰኑ የትምህርት አይነቶች ያገኟቸውን ውጤቶች ማጣራትን የሚጠይቅ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ኤጀንሲው በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የእነዚህ ተማሪዎች ውጤት በተለዩት የትምህርት ዓይነቶች ብቻ ውጤታቸው ተይዞ ተጨማሪ ማጣራት እንዲደረግበት ወስኗል፡፡ ስለሆነም ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው አካላት በተውጣጣ ግብረሃይል የሚያደረገው የማጣራት ስራ እንዲሳካና የጀመረውን የትምህርት ጥራት የማስጠበቅ ጅምር ስራ እንዲጠናከር የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እንዳይለይው በመጠየቅ፣ ለመላ ተማሪዎች በሙሉ መልካም የትምህርት ዘመን እንዲሆን ይመኛል፡፡

ነሐሴ 7 ቀን 2011 ዓ.ም.

አዲስ አበባ